***<u>ከሦስት ዓመት በፊት ከቀድሞ ቅንጅት አባላት ጋር በአባሪነት በቁጥጥር ስር ውለው የነበሩ እና የዋስትና መብታቸው ከተነፈጉት እስረኞች መሀከል የሆኑት አቶ ገድሉ አየለ በማረሚያቤት እንዳሉ ህይወታቸው አለፈ።</u>***

**ምርጫ 97ን ተከትሎ በተነሳ ብጥብጥ ታህሳስ 16 1997 ለመጀመሪያ ጊዜ በቁጥጥር ስር የዋሉትና «የምርጫው ውጤት ከታወቀ በኃላ ድርጅቱ የተከተለውን ሕገመንግስቱን በሀይል የማፍረስ ሙከራ በሕቡእ እና በትጥቅ የተደገፈ አመፅ አቅደዋል፣ በሚች ቅጣው እጅጉ ከተቋቋመውና ራሱን ኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ አንድነት ግንባር ወይም የአርበኞች ግንበር በሚል ስያሜ በሚጠራ ሕገወጥ ድርጅት ስር በትጥቅ ትግል የሚደገፍ አዲሱ ቅንጅት በሚል የአመፅ ትግል ለማካሄድ ተንቀሳቅሰዋል» በሚል ክስ የተመሰረተባቸው አቶ ገድሉ እስከ መጋቢት ወር ድረስ በወንጀል ምርመራ በእስር እንዲቆዩ ተደርገው ነበር። ፖሊስ በወቅቱ መረጃ አሰባስቦ ክስ መመስረት ባለመቻሉ ፍርድ ቤት በውጭ ሆነውና እንዲከታተኩ ወስኖላቸው ነበር።ይሁንና በድጋሚ በግንቦት 22 ቀን ተይዘው በቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዲታሰሩ ተደርገዋል።**

**አቶ ገድሉ ከቅንጅት ተከሳሾች ጋር በተመሳሳይ ፋይል ጉዳያቸው ሲታይ ቆይተው በመጨረሻ እርሳቸውና ሌሎች 50 ሰዎች ጉዳያቸው ከአርበኞች ግንባር ጋር ይያያዛል ተብሎ ክሳቸው እንዲይ እንደተደረገ አብረዋቸው በእስር የነበሩ ግለሰብ ገልፀውልናል። ከነዚህ ተከሳሾች መሀከል 28 ሰዎች በዋስ ሲለቀቁ አቶ ገድሉን ጨምሮ 9 ሰዎች የዋስትና መብታቸው ተከልክሎ በማረሚያቤት እንዲቆዩ ተደርገዋል።**

**አቶ ገድሉ በማረሚያ ቤት ሆነው ክሳቸውን በመከታተል ላይ እያሉ ነው በሀምሌ 8 2000 ዓ.ም ህይወታቸው ሊያልፍ የበቃው። መሟች አቶ ገድሉ የ38 ዓመት ጎልማሳ፣ የአዲስ አበባ ነዋሪና የሁለት ልጆች አባት ነበሩ።**

**ከነአቶ ገድሉ ጋር በአንድ ፋይል ከተከሰሱ 50 ሰዎች መሀከል እስካሁን በእስር ላይ እያሉ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ሶስት ደረሷል። ከወር በፊት አርጋታ ጎበና የተባሉ ተከሳሽ ያረፉ ሲሆን በማእከለዊ እያሉ አቶፀጋዬ አየለ የተባለ ወጣት በድብደባ መሞቱን በእስር ቤት አብረው ከነበሩት ግለሰብ ለመረዳት ችለናል።**

**እንደ ምንጫችን ገለፃ ፍርድ ቤት ብይን ለመስጠት ለሐምሌ 25 ተለዋጭ ቀጠሮ ተሰጥቶአቸው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።**